Government of Western Australia
Department of Health

Amharic

# ልጆች ያሉበትን ተሽከርካሪ ከሲጋራ ጪስ የፀዳ ማድረግ

ከ22 ሴፕቴምበር 2010 ጀምሮ አዲስ የወጣ የሲጋራ ማጨስ ማእቀብ

## ልጆች በሚጓዙበት ተሽከርካሪ ውስጥ ሲጋራ ማጨስ የተከለከለ ነው።

### በምእራብ አውስትራሊያ በተሽከርካሪ ላይም ሆነ ውስጥ እድሜአቸው ከ17 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ባሉበት ሲጋራ ማጨስ ታግዷል።

ግለሰብ በመኪና ላይም ሆነ ውስጥ በሚከተሉት ሁኔታዎች ማጨስ አይችልም —

- ማኪናው በመንገድ ላይ ከሆነ፤ እና
- በተሽከርካሪው ውስጥ ወይም ላይ ልጆች ካሉ።

**ልጅ**
ማለት እድሜው 17 ያልደረሰ ማንኛውም ወንድ ወይም ሴት ልጅ ማለት ነው

**ተሽከርካሪ**
ማለት ሰዎችን ወይም እቃን በመንገድ ላይ ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መጓጓዣ ማለት ነው

**መንገድ**
ማለት ማንኛውም ለሕዝብ ጥቅም ክፍት የሆነ አውራ ጎዳና፤ ጎዳና ወይም መንገድ ማለት ሲሆን፤ ማንኛዎንም ሁለትዮሽ መንገድ፤ የእገር መንገድ፤ የተከለለ ሥፍራ፤ በመንገድ መካከል የሚገኝ ሥፍራን እና የትራፊክ ደሴቶችን እንዲሁም የሕዝብ መኪና ማቆሚያዎች ያጠቃልላል።

### ተፈጻሚነት

- ከጤና ክፍል ጋር በመተባባር ልጆች ባሉበት ተሽከርካሪ ውስጥ ሲጋራ ማጨስን በተመለከተ፤ ፖሊሶች ደንቡን ተፈጻሚ ማድረግ ይችላሉ።.
- ይህንን አዲስ ሕግ የሚተላለፉትን ግለሰቦች ፖሊሶች ተሽከርካሪውን በማስቆም ዝርዝር መረጃ መመዝገብ ይችላሉ። ከዚያም ዝርዝሩን ለትንባሆ ቁጥጥር ቅርንጫፍ ቢሮ ሁኔታውን ተከታትሎ ፤ ማስጠንቀቂያ፤ መቀጫ ወይም ለፍርድ እንዲቀርቡ እርምጃ እንዲወሰድ ያስደርጋሉ።

ይህንን ጉዳይ አጽንኦት መስጠት ያስፈለጋል፤ ምክንያቱም ደንቡ ሲደነገግ የህዝብ ከፍተኛ ድጋፍ ነበረው። ካለፉት ልምዶች እንደምንረዳው፤ አብዛኛዎቹ የምእራብ አውስትራሊያ ኗሪዎች ደንቡን ተፈጻሚ እንደሚያደርጉት ይጠበቃል።

### መቀጮ

እድሜው ከ17 ዓመት በታች የሆነ ልጅ ባሉበት ተሽከርካሪው ውስጥም ሆነ ውጭ የሲጋራ ያለማጨሱን ደንብ በተላለፈ ግለሰብ ላይ የሚከተሉት መቀጮዎች ይጣሉበታል፤

| | |
|---|---|
| በፍርድ ቤት የሚጣለው ከፍተኛው መቀጮ | $1000 |
| ደንቡን የመተላለፍ ማስጠንቀቂያ | $200 |

ለተጨማሪ መረጃ የትንባሆ ቁጥጥር ቅርንጫፍ ቢሮን ያነጋግሩ፤
ስልክ ቁጥር: 1300 784 892
ኢሜል: tcb@health.wa.gov.au

**Disclaimer:**
The information contained in this factsheet has been produced as a guide only.
To view the full details in the relevant Tobacco Control legislation, visit www.health.wa.gov.au/tobaccocontrol

HP 11901 OCT'10